የሰ/መ/ቁ. 46382

ሐምሌ 28 ቀን 2001 ዓ.ም.

**ዳኞች** ፡- ዓብዱልቃድር መሐመድ

ሐጎስ ወልዱ

ሂሩት መለሠ

ታፈሠ ይርጋ

በላቸው አንሺሶ

**አመልካች** ፡- 1. ዳንኤል ገ/ዮሐንስ
2. ሚካኤል ፀጋዬ
3. ሚ/ር አሚት አብዶ
4. ቅዱስ ዓለምሰገድ
} ጠ/ማሪን ወንዴ

**ተጠሪ** ፡- ፌዴራል ዐቃቤ ሕግ - ተሾመ አንጄሎ

መዝገቡ ተመርምሮ ቀጥሎ የተመለከተው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

**ፍ ር ድ**

ይህ ጉዳይ የወንጀል ክርክር ሲሆን ተጠሪ በፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በአመልካቾች ላይ ያቀረበው የወንጀል ክስ የወንጀል ሕግ ቁጥር 32/1/ሀ/ እና 692/1/ ላይ የተመለከተውን በመተላለፍ ሚያዝያ 16 ቀን 2001 ዓ.ም. ከምሽቱ 4፡45 ሲሆን በአዲስ አበባ ከተማ በቂርቆስ ክፍለ ከተማ ቀበሌ 15/16 ክልል የግል ተበዳይ አቶ ኢሳያስ ካሣ ግሮሰሪ በመሄድ ውስኪ እንፈልጋለን ብለው መኪና ውስጥ ሆነው አንድ ብላክ ሌብል ውስኪ አዘው እሱን ከተመለከቱ በኂላ ሌላ ብላክ ሌብል ጨምረን ብለው ሲጨምርላቸው ሲሄድ መኪና አስነስተው በማምለጣቸው ተከሰዋል የሚል ነው፡፡

አመልካቾች ቀርበው ክሱ ተነቦላቸው እንዲረዱት ከተደረገ በኂላ በክሱ ላይ መቃወሚያ እንዳላቸው ተጠይቀው ክሱን እንደማይቃወሙ ካረጋገጡ በኂላ የዕምነት ክህደት ቃል ሲጠየቁ ድርጊቱን ፈፅመናል ጥፋተኛም ነን ብለዋል፡፡

ፍ/ቤቱም በወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ሥነ ሥርዓት ቁጥር 134/1/ መሠረት የጥፋተኛነት ውሣኔ ከሰጠ በኂላ የግራ ቀኙን የቅጣት አስተያየት ተቀብሏል፡፡ በዚህም መሠረት ከሣሽ ዐቃቤ ሕግ በሰጠው የቅጣት አስተያየት ተከሣሾች የወንጀሉን ድርጊት የፈፀሙት ግብረአበር በመሆን ስለሆነ ፍ/ቤቱ ይህንን በቅጣት አወሳሰን ረገድ ከግምት እንዲያስገባልን ካለ በኂላ ተከሣሾች የትምህርት ደረጃቸው ሲታይ የወንጀልን አስከፊነት ከሌላው ሰው በተሻለ መልኩ ሊያውቁና ሊረዱ የሚችሉ መሆኑን መገንዘብ ስለሚቻል ይህንንም ከግምት በመክተት እንደዚሁም ፍ/ቤት ቀርበው ማመናቸውንም ከግምት በማስገባት ፍ/ቤቱ ተገቢ ነው ብሎ ያመነበትን ቅጣት እንዲወስንባቸው በማለት አመልክቷል፡፡

ተከሣሾችም በበኩላቸው ድርጊቱ በአጋጣሚ የተፈፀመ መሆኑን፣ ወጣቶች እንደሆኑ፣ በድርጊታቸውም እንደተፀፀቱና ከግል ተበዳይም ጋር እንደታረቁ ገልፀው የከፍተኛ ትምህርት ተማሪዎች መሆናቸውን ጠቅሰው ቅጣቱ በገደብ እንዲሆን ይወሰንልን በማለት የቅጣት አስተያየት መስጠታቸውን ተገንዝበናል፡፡

በዚህ መልኩ የቅጣት አስተያየት የቀረበለት የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤትም ተከሣሾች የተከሰሱበት ወንጀል እስከ 3 ዓመት በሚደርስ እሥራት የሚያስቀጣ ቢሆንም ተከሣሾች አስቀድሞ ወንጀል የፈፀሙ ስለመሆኑ ሪከርድ ያልቀረበባቸው ስለሆነና ይህንንም ወንጀል ስለመፈፀማቸው ያመኑ በመሆኑ ይህም ሁኔታ በወንጀል ሕግ ቁጥር 82/1/ሠ/ መሠረት

ቅጣት ማቅለያ ተደርጎ ሊወሰድ ስለሚችል ተከሣሾች እያንዳንዳቸው በ6 /ስድስት/ ወር ቀላል እስራት እንዲቀጡ በማለት ውሣኔ ሠጥቷል፡፡

ተከሣሾች የጥፋተኛነት ውሣኔውን ተቀብለው ነገር ግን በቅጣት ማቅለያነት ያቀረቡት ምክንያቶች የተወሰነውን ቅጣት በወንጀል ሕግ ቁጥር 192 መሠረት በገደብ ለማቆየት የሚያስችል ሆኖ ሳለ ቅጣቱ ሳይገደብ መቅረቱ ተገቢነት የሌለው ነው በማለት የይግባኝ ቅሬታቸውን ለፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት አቅርበው ፍ/ቤቱም በበኩሉ ግራ ቀኙን አከራክሮ የሥር ፍ/ቤት ውሣኔ ጉድለት የሌለው ነው በማለት አጽንቶታል፡፡

የሰበር አቤቱታውም የቀረበው ይህንኑ በመቃወም ሲሆን ይህም ችሎት አቤቱታውን መርምሮ በአመልካቾች ላይ የተወሰነውን ቅጣት በገደብ ለማቆየት የሚያበቃ ሁኔታ ስለመኖሩ ለማጣራት አቤቱታው ለሰበር ችሎት ይቅረብ ብሎ ግራ ቀኙን አከራክሯል፡፡

በአጠቃላይ የክርክሩ ይዘት ከፍ ብሎ የተጠቀሰው ሲሆን በበኩላችንም አቤቱታው ለሰበር ይቅረብ ከተባለበት ነጥብ አኳያ እንደሚከተለው መርምረነዋል፡፡

በአንድ የወንጀል ተከሣሽ ላይ የጥፋተኛነትና የቅጣት ውሣኔ ከተሰጠ በኋላ የተወሰነው የእሥራት ቅጣት ሳይፈፀም በገደብ እንዲቆይ ሊደረግ የሚችልባቸው ምክንያቶች በወንጀል ሕግ በቁጥር 192 ላይ ተመልክቶ ይገኛል፡፡ እንደዚሁም የቅጣት ውሣኔ በገደብ ሊቆይ የማይችልባቸው ምክንያቶችም በቁጥር 194 ሥር ተመልክቷል፡፡

በዚህም መሠረት ከቁጥር 192 አኳያ የተወሰነውን የእስራት ቅጣት በገደብ ለማቆየት የሚቻለው ጥፋተኛው አስቀድሞ የተፈረደበት ቢሆንም ባይሆንም የተፈረደበትን ቅጣት ከመፈፀሙ በፊት ለተወሰነው ጊዜ ቅጣቱ ታግዶለት አመሉ ቢፈተን ሁለተኛ ጥፋት ከማድረግ የሚታገድ መሆኑንና ስለጠባዩም መሻሻል አንድ ጽኑ ማስጠንቀቂያ ብቻ የሚበቃ መሆኑን ፍ/ቤቱ ያመነበት ከሆነ ነው፡፡ በተያዘው ጉዳይ አመልካቾች ቀደም ሲል ወንጀል ስለመፈጸማቸው ሪከርድ ያልቀረበባቸው እንደመሆኑ መጠን ያለፈ የሕይወት ታሪካቸው መልካም እንደነበር ይገመታል፡፡ አሁን ጥፋተኛ ሆነው የተገኙበትንም ወንጀል በየዋህነት ወይም ባልታሰበና ድንገተኛ አጋጣሚ የፈፀሙት ስለመሆኑ መገንዘብ ይቻላል፡፡ ከዚህም ሌላ አመልካቾች ወንጀሉን ከፈፀሙ በኋላ ከግል ተበዳዩ ጋር ወዲያውኑ መታረቃቸው ድርጊቱን በድንገተኛ አጋጣሚ በየዋህነት የፈፀሙት መሆኑና በዚህም መጸጸታቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ በሌላ በኩልም የወንጀል ሕግ ግብ በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 1 ላይ የተመለከተ ሲሆን ይዘቱም የወንጀል ሕግ ግብ ወንጀል እንዳይፈጸም መከላከል ሲሆን ይህንን የሚያደርገው ስለወንጀሎችና ስለቅጣታቸው በቅድሚያ ማስጠንቀቂያ በመስጠት ማስጠንቀቂያነቱ በቂ ባልሆነበት ጊዜ ወንጀል አድራጊዎቹ ተቀጥተው ሌላ ወንጀል ከመፈፀም እንዲቆጠቡና ለሌሎች ማስተማሪያ እንዲሆኑ ወይም እንዲታረሙ በማድረግ ወይም ተጨማሪ ወንጀሎች እንዳይፈፀሙ ዕርምጃዎች እንዲወሰድባቸው ማድረግ እንደሆነ ተመልክቷል፡፡

የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በወንጀል ሕግ ቁጥር 82 መሠረት ቅጣቱን በማቅለል ከወሰነ በኋላ አመልካቾች ከፍ ብሎ እንደተመለከተው የቀድሞ የወንጀል ሪከርድ ያልቀረበባቸው ከመሆኑ አኳያ ይህንንም ወንጀል የፈፀሙት በድንገተኛ አጋጣሚ በየዋህነትና ባለማስተዋል ከመሆኑ አንፃር በአጠቃላይም ከወንጀል ሕግ ግብ አኳያ ሲታይ አንድ ጽኑ ማስጠንቀቂያ ብቻ ተሰጥቷቸው የተወሰነባቸው ቅጣት ሳይፈፀም ተግዶ ቢቆይ ዳግም ጥፋት ከመፈፀም ሊታቀቡ እንደሚችሉ ከአጠቃላይ የወንጀሉ አፈፃፀምና ከአመልካቾች ሁኔታ መገንዘብ እየተቻለና ቅጣቱንም በወንጀል ሕግ ቁጥር 194 መሠረት በገደብ ላለማቆየት የሚያበቃ ምክንያት በሌለበት ሁኔታ ቅጣቱን ለመገደብ የሚያበቃ በቂ ሕጋዊ ምክንያት እያለ እንዲገደብ ሳያደርግ መቅረቱ የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤትም ይህንኑ ሳያርም መቅረቱ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

## <u>ው ሣ ኔ</u>

1. የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በወ/መ/ቁ/7933 በ21/8/2001 ዓ.ም. የሰጠውን የጥፋተኛነትና የቅጣት ውሣኔ እንደዚሁም የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይህንኑ በማጽናት በመ.ቁ. 45568 በ9/9/2001 ዓ.ም. የሰጠውን ውሣኔ በበኩላችንም በማጽናት ነገር ግን በአመልካቾች ላይ የተወሰነው የ6 /ስድስት/ ወር ቀላል እሥራት ከፍ ብሎ በተመለከቱት ምክንያቶች ሳይፈፀም በ2 /ሁለት/ ዓመት ገደብ ይቆይ በማለት በወንጀል ሕግ ቁጥር 192 እና 197/1/ መሠረት ወስነናል፡፡

2. በአመልካቾች ላይ የተወሰነው የእስራት ቅጣት የተገደበ ስለመሆኑ እንዲታወቅ ለሥር ፍ/ቤቶችና ለአ.አበባ ማረሚያ ቤት ይገለጽለት ብለናል፡፡
3. አመልካቾች በዚህ ችሎት ክርክር ሲደረግ እያንዳንዳቸው ለዋስትና በሞዴል 85 ያስያዙት ብር 2000 /ሁለት ሺህ/ እንዲመለስላቸው ለሚመለከተው ይፃፍ ብለናል፡፡
4. መዝገቡን ዘግተን ወደ መ/ቤት መልሰናል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ጽ/ሽ